4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር____________
ቀን ጥቅምት ፴፣ ፳፻
Date 11/10/2007

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አህዱ አምላክ አሜን**

**በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ-ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት አገር የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በአዲሱ ዕስራ ምዕት ዓመት የመጀመሪያው የሆነውን ፳፩ኛ መደበኛ ጉባዔውን በኮለምበስ ኦሃዮ ከጥቅምት ፳፯ እስከ ከጥቅምት ፴ ፳፻ ዓ.ም. በተለያዩ መንፈሳዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ሲያካሂድ ቆይቶ በመጨረሻ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።**

**<u>መግቢያ</u>**

የሦስት ሺህ ዓመታት ረዥም ታሪክ ባላት በታላቂቱ ሀገር በኢትዮጵያ የእምነት፣ የመንግሥታዊ መዋቅር፣ የባህልና የሥልጣኔ ማዕከል በመሆን የምትታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን ትውፊቷንና ሐዋርያዊ ሥርዓቷን ጠብቃ ወደ ሶስተኛው ሺህ የእምነትና የታሪክ ምዕራፍ ስትሸጋገር፤ ከሁሉ አስቀድማ “ክብርና ምስጋና ሁሉን ለሚችል ለእግዚአብሔር ይሁን” ትላለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን ሕጋዊ ሲኖዶስ ባለፉት ፪ሺህ ዓመታት በመላው ኢትዮጵያ ለክርስትና እምነት የደከሙ፤ በወንጌል አገልግሎት መንፈሳዊ ሥራና ታላላቅ ምግባራትን ለፈፀሙ፤ በእምነት ሰማዕትነትን ለተቀበሉና በመንፈሳዊ ተጋድሎ ቤተ ክርስትያኗን በፅናት ላቆዩልን አባቶቻችን እና እናቶቻችን፤ ኢትዮጵያዊያን ፃድቃን ሰማዕታት በሙሉ የዚህ ትውልድ ምስጋና ይድረሳቸው ትላለች።

በዚህ በሦስተኛው የዕስራ ምዕት መግቢያ ላይ ለቀደሙ መንፈሳዊ አባቶቻችንና እናቶችን ድካም ዋጋ መስጠት፣ አሁን ላለው ትውልድ ጥለው ያለፉትን መልካም አርአያነት በማስተዋል እየመረመሩ በሥራ እነርሱን መምሰልና ከተግባራቸው መማር ለዛሬው ትውልድ ችግሮች መፍቻ ፍቱን መድኃኒት ነው ብሎ ቅዱስ ሲኖዶስ ያምናል።

ባለፉት ፪ሺህ ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ በህልውናውና አንድነቱ ላይ ያልወደቀ መከራና የፈተና ዓይነት አልነበረም። ሕዝባችን ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚነሱበትን ፈተናዎች እንደየአመጣጣቸው በመቋቋምና ችግሮችን በመፍታት ሕልውናውን ጠብቆ የቆየው ከባህልና ከመንፈሳዊ እምነት በመነጨ የፍቅር፣ የመቻቻል፣

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር____________
ቀን ጥቅምት ፴፣ ፳፻
Date 11/10/2007

የመተባበርና ስለ ሀገር ሲሉ የግል ስሜትንና ጥቅምን ወደ ጎን በመተው አብሮ የመኖር ዘዴዎችን ዋነኛ መሣሪያ በማድረግ ነው።

የሃይማኖት አባቶቻችንና እናቶቻችን አሁን የምንገለገልበትና የምንኮራበትን ብሔራዊ የሆነው የቀን መቁጠሪያ ያበረከቱልን፣ የፅሁፍና የፊደል ፀጋ ባለቤት ያደረጉን፣ ዓለም ለምርምር የሚደክምባቸውን በራሳችን ቋንቋና ፊደል የተጻፉ ሥነ-ፅሁፎች ክምችቶችን በሠፊው የተዉልን፣ የዓለም ሊቃውንት፣ ተጓዦችና ሀገር ጎብኚዎች ሳይቀር የሚደነቁባቸው የሥልጣኔና የሥነ-ጥበት መለኪያ የሆኑ ጥንታዊያ ሥነ-ሕንፃና ታሪካዊ ቅርሳ ቅርሶችን ከነፃነት ጋር ያወረሱን እንደዛሬው ቴክኖሎጂና የመገናኛ ብዙሃን ኖሯቸው፤ ፈጣን የመጓጓዣና የሳታላይት መረጃዎች ተጠቅመው ሳይሆን ለግል ስሜት ሳይሸነፉ በቅን ልቦናና በመተሳሰብ አብረው ስለሠሩ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላካዊ የእርቅ ተልዕኮ አበክራ ስታስተምር የኖረች እንደመሆኗ፣ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በወንድማማቾች እና እህታማማቾች መሀል ደም መፋሰስ እንዳይኖር፣ የተራራቁትን በማቀራረብ፣ የተለያዩን በማስታረቅ የብኩላን አስተዋፅዖ ስታበረክት ኖራለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን “ይቅር ለእግዚአብሔር”፣ “ሽምግልና”፣ “እርቅ”፣ “ስለ እገሌ ትቻለሁ” … ወዘተ የሚባሉት የቅራኔና የግጭት ማርገቢያ ቃላቶች ቦታ እያጡ መምጣታቸው የሕዝባችን አብሮ የመኖርና የአንድነት ኃይል እየተሸረሸረ መምጣቱን የሚያመለክቱ ናቸው።

ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን ዓቢይ ጉዳይ በስፋት ከመረመረ በኋላ በዚህ የፈተና ዘመን ላይ ቤተ-ክርስትያኗ ለሕዝብ አንድነት የሚጠበቅባትን ሚና እንዳትዘነጋ እና ምን መደረግ እንዳለበት በተለይም በውስጧ ያለውን መከፋፈል በተመለከተ ሰፊ ውይይት አድርጎበታል።

ስለዚህም በስደት የሚገኘው ይኸው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ለሰላምና ለአንድነት ያለውን አካሄድና አቋም ለመላው ኢትዮጵያውያን በግልጽ ማስታወቅን መርጧል። በመሠረቱ ቅዱስ ሲኖዶስ ከመነሻው፣ “ሕግ ፈረሰ - ቀኖና ተጣሰ!” ብሎ በሰፊው ለሕዝብ ለማስረዳት ሰፊ የሆነ የመናገር ነጻነት፣ ነፃ ፕሬስና የብዙኃን መገናኛ ወዳለበት ሀገር ከተሰደደበት ጊዜ ጀምሮ ሰላምንና አንድነትን በመሻት፣ ስለ ሰላምና ችግሮችን ተወያይቶ ስለ መፍታት ከመናገር የቦዘነበት ጊዜ የለም።

በዚህ አጋጣሚ፣ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ለተቋቋሙት የበጎ ፈቃድ አስታራቂዎችና ሽማግሌዎች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ በበጎ ፈቃዳቸው የተቋቋሙትን የእርቅ

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር____________
ቀን ጥቅምት ፴፣ ፳፻
Date 11/10/2007

ኮሚቴዎች በሊቀ መንበራቸው በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ አማካኝነት የአባቶች ምስጋና እንዲተላለፍላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል።

ሕጋዊውን ቀኖና ጠብቆ በውጭ ሀገር የቆመው ይኸው ሲኖዶስ፣ በተለይ ጳጳሳት መሾም በጀመረበት ጊዜ የተደናገጡና ልዩ ስሜት ያደረባቸው ወገኖች አላስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ፣ ሲኖዶሱ የሰላም እጁን በመዘርጋት ለእርቅ በሩን ክፍት አድርጎ እንነጋገር በማለት ያሳየው ቀናነት አይዘነጋም። በሁለቱም ሀገሮች የሚገኙ ኮሚቴዎች፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን አንድ እንድትሆን አባቶች እንዲገናኙና እንዲወያዩ፣ እርቅ እንዲወርድ በተጠየቁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህ በውጭ ሀገር የሚገኘው ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ፈጥኖ የበጎ ፈቃድ ምላሽ ሲሰጥ የቆየ መሆኑን ስንገልጽ፣ አሁንም ቢሆን በሀገር ውስጥ ካሉት የሃይማኖት በኩል በዚህ መንፈስ ለሚመጣ በጎ ምላሽ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ መሆናችን ሕዝብ እንዲያውቀው ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል።

በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ለቤተ-ክርስትያኗ አንድነትና ሰላም በስደት የሚገኘው ሲኖዶስ የተለየ ፀሎት ከማድረግና በአርዓያነት አንድ እርምጃ ወደፊት ከመሄድ ተቆጥቦ አያውቅም። ስለሆነም በክርስቶስ መስቀል ስር፣ እንኳንስ ወንድማማቾችና የአንድ ሀገር ልጆች፤ ባዕዳንም ቢሆኑ የእርቅ ፈለግን ሊከተሉ መንፈሳዊ ትምህርታቸው ግድ ይላቸውልና ስለ ስላምና አንድነት እንደእኛ ሁሉ ሌሎችም እጃቸውን እንዲዘረጉ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያስተላልፋል።

## <u>ቅዱስ ሲኖዶስ በጽናት የተመለከታቸው ወቅታዊ ጉዳቶችና አሳሳቢ ችግሮች</u>

ከዘመን ወደ ዘመን እየከፉ በመጡት የኢትዮጵያ ወቅታዊ ችግሮችና አሳሳቢ ጉዳዮች ዙሪያ ቅዱስ ሲኖዶስ ሠፊ ውይይት በማድረግ የሚከተሉትን ነጥቦች በዋናነት ተመልክቷል።

1. ባልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታና ማህበራዊ ችግሮች በስደት ከሀገር የሚወጡ ዜጎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መሄድና ከድንበር መሻገር ጀምሮ በመላው ዓለም ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ለድንገተኛ አደጋ፣ ለሕገ-ወጥ ጥቃት፣ ለእንግልትና ስቃይ የመዳረጋቸው ሁኔታ እንደቀጠለ ነው። በተለይ በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ በየጊዜው የሚፈፀሙት በደሎች እየተባባሱ ከመምጣታቸው ጋራ፣ ፍፁም ተቆርቋሪና አለኝታ የሌላቸው ሆነው መታየታቸው በአሳዛኝ መልኩ ቀጥሏል።

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር____________
ቀን ጥቅምት ፴፣ ፳፻
Date 11/10/2007

2. ኢትዮጵያ ከድህነትና ቀደም ካሉት ጦርነቶች ገና ሳታገግም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በምስራቅ እና በሰሜን የገባችበት ፍጥጫና ውጥረት ለአዲስ ዙር የደም መፋሰስና የሰላም መደፍረስ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ስጋቱ እያየለ መጥቷል። ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በሁለቱ አቅጣጫ እያንዣበበ የመጣውን ሁኔታና ኢትዮጵያውያን የሚከፍሉትን መስዋዕትነት በማጤን መዘዙን አስጊ ሆኖ አግኝቶታል።

3. የሱዳን መንግሥት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጎችን ጥሶ ለዓመታት አስሮ ያቆያቸው ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ የፖለቲካ ወገኖች በቅርቡ አሳልፎ ለኢትዮጵያ መንግሥት በመስጠት በኢትዮጵያውያን ዜጎች ላይ የፈጸመው በደል ሌላ የቅርብ አሳዛኝ ክስተት ነው።

4. መከራን በመሸሽ ተሰድደው ኬንያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ላይ በቅርቡ እየተፈፀመ ያለው አሰቃቂ ግድያና አፈና፣ ሕሊና ላለው ዜጋ ሁሉ እንቅልፍ የሚነሳ መሆኑ አያጠራጥርም። ይህ በኢትዮጵያውያን የሚፈፀመው የነፍስ ግድያ በየትኛውም ዘመን ያልታየ ጭካኔ ከመሆኑም በላይ ለሰላም መደፍረስ ምክንያት መሆኑ አይካድም።

5. ከጥቂት ወራት በፊት የኢትዮጵያ መንግሥት በአስታራቂ ሽማግሌዎች አመካኝነት የፖለቲካና የሕግ እስረኞችን በመፍታት ያሳየው መልካም ጅምር የሀገሪቱን የ፪ሺህ ዘመን መባቻ አስታኮ ታሪኳንና ባህሏን ለዓለም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ያደረገው ጥረት የሚያበረታታ ተግባር እንደሆነ አይካድም። ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ እርምጃ ለአጭር ጊዜ የፖለቲካ ፍጆታ ከመሆን አልፎ ለሀገሪቱ ሠላምና ጥቅም በዘለቄታዊነት እንዲቀጥል ለማድረግ ገዥው ፓርቲ በዚህ ረገድ ያለውን ኃላፊነት መወጣትና በቀጣይም ለብሄራዊ እርቅ መዘጋጀት እንዳለበት ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ይመክራል።

6. በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በመወዳደር ከላይ የተጠቀሱትን የሀገሪቱን ወቅታዊና የቆዩ ችግሮች ለመፍታት ይችላሉ ተብለው ሕዝብ ያመነባቸውና በግንቦት 1997 ምርጫ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች የመከፋፈል ሁኔታ ሕዝቡን ያሳዘነ መሆኑን ጉባኤው በሰፊው ተመልክቷል።

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር____________
ቀን ጥቅምት ፴፣ ፳፻
Date 11/10/2007

በአጠቃላይ ከላይ የተነሱትን ነጥቦችና ወቅታዊ ጉዳዮች በሰፊው ከተመለከተ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

## መግለጫ

1. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እያንዣበበ ያለው የጦርነት ደመና በረሀብ፣ በብሽታና በድህነት ተጠቂ የሆነውን ሕዝባችን ለከፋ ጉዳት የሚዳርግና የብዙ ዜጎችን ሕይወት የሚቀጥፍ ስለሆነ ችግሩን በሠላማዊ ድርድር ለመፍታት ሁለቱም መንግሥታት ትዕግስት እንዲገዙ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል። የእስካሁኑ ደም መፋሰስና ዕልቂት እንዲሁም ለጦርነት የባከነው ሀብትና ንብረት ከተገቢው በላይ ሆኖ ሳለ፣ ሁለቱም ወገኖች ማቆምያ ወደሌለው ተጨማሪ ጦርነት ለመግባት የሚደርጉትን ጥድፊያ አቁመው ለሰላማዊ ድርድር የጠየቀውን ያህል መስዋዕትነት እንዲከፍሉ ቅዱስ ሲኖዶስ አበክሮ ይጠይቃል።

2. በሀገራችን ምሥራቃዊ ክፍል በሚገኘው በኦጋዴን አካባቢ ያለው አለመረጋጋት ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ በመንግሥትና በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ውይይት ቢካሄድ አላስፈላጊ የሆነውን ደም መፋሰስ ሊያስቀረው የሚችል ከመሆኑም በላይ፣ ለክልሉ መረጋጋትና ዘላቂ ሰላም አስተዋፅዖ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል። ስለሆነም ሁሉም ወገኖች ለሰላም ቅድሚያ እንዲሰጡ ቅዱስ ሲኖዶስ ይጠይቃል።

3. የሱዳን መንግሥት ባልታወቀ ምክንያት አስሮ ያቆያቸውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃዋሚ ወገኖች ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳልፎ መስጠቱ በዜና ማሰራጫዎች ይፋ ሆኗል። ይህ ዓለም አቀፍ ሕግን የጣስ ድርጊት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የእስረኞች ዘመዶችንና ሌላውንም ሕዝብ እያስጨነቀ የሚገኝ በመሆኑ የዓለም የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ክትትል እንዲያደርጉ ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንኦት ይጠይቃል።

4. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኬንያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ አፈና እና ግድያ እየተፈፀመ መሆኑ የሲኖዶስ አባላትን በእጅጉ አሳዝኗል። ስለሆነም የዓለም መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ደህንነትና ሕልውና የማስጠበቅ ታላቅ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፣ ጉዳዩን በማጣራት ወንጀል ፈፃሚዎች ለፍርድ ለማቅረብ ሕጋዊ ክትትል እንዲያደርጉ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር____________
ቀን ጥቅምት ፴፣ ፳፻
Date 11/10/2007

5. ለዲሞክራሲ፣ ለነጻነትና ለብልጽግና መልካም አርአያ ይሆናሉ፤ ሀገርን ይመራሉ ተብሎ አዲሱ ትውልድ ተስፋ የጣለባቸው ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ድርጅቶች በቅርቡ ያሳዩት አለመግባባት ቅዱስ ሲኖዶስ እጅግ አሳዛኝ ሆኖ አግቶታል:: ብዙ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታትና ረዥም ጉዞ ለመጓዝ የተቀናጀው ይህ በርከት ያሉ ምሁራንን ያሰባሰበ የፖለቲካ ፓርቲ በውስጡ የተከሰቱ ጥቃቅን አለመግባባቶችን በውይይት መፈታት የማይችል ሆኖ መገኘቱ የሕዝቡን ቅስም የሰበረ በመሆኑ የአመራር አባላቱ በአስቸኳይ ተሰብስበው ነባር የሆነውን ባሕላዊ የዕርቅ ሥርዓት በመከተል ችግራቸውን እንዲፈቱና ወደ አንድነት እንዲመለሱ ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል::

6. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚገኙ የዜና ማሰራጫዎች፣ በአዲሱ የእስራ ምዕት ዓመት ለሰላምና ለእርቅ የሚያግዙና ጥላቻንና መለያየትን የሚያስወገዱ መልዕክቶችን በማቅረብ ሙያዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ ሕዝቡም መቻቻልን ባሕል አድርጎ በማስተዋል እንዲራመድና በማናቸውም ሁኔታ የሚፈጠሩ ልዩነቶችን ሁሉ በሰከነ መንፈስ እንዲፈታ ቅዱስ ሲኖዶስ ይመክራል::

7. መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ሀገሪቱ የምትገኝበትን ሁኔታ በማጤን እየከረረ የሄደውን ውጥረትና የዜጎች መከራ ለማቆም እንዲችል ከምንም በላይ ተስፋና ጉልበታችን እግዚአብሔር አምላካችን ነውና፣ እያንዳንዱ ዜጋ ስለ ሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ እጁን ወደ እግዚአብሔር እንዲዘረጋና በፀሎትና በምህላ እንዲተጋ ቅዱስ ሲኖዶስ በታላቅ አደራ ያሳስባል::

በተዘጋ በር ገብቶ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" በማለት በጭንቀት ላይ የነበሩ ደቀመዛሙርቱን ያረጋጋ ጌታ መድኃኒታችን ክርስቶስ ዛሬም "ሰላም ለኢትዮጵያ!" ሰላም ለዓለም ሁሉ የሚል ድምጹን ያሰማን፣ አሜን::

ጥቅምት ፴፣ ፳፻ ዓ.ም
ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ

ኮሎምቦስ ኦሃዮ

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

**ቁጥር**_____________
**ቀን ጥቅምት ፴፤ ፳፻**
Date 11/10/2007